# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው

ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): M. Maillot; Tammy S.

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2017 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው፡፡


አንድ ሌሊት
እግዚአብሔር
አብርሃምን አዲስ
ነገር ተናገረው።


ይህም ልጁን ወይንስ
እግዚአብሔርን
አብልጠ እንደሚወድ
ለመፈተን ነበር።

የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን
መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው
አለ። ይህ ለአብርሃም
እጅግ ከባድ ጥያቄ
ነበር። ምክንያቱም
ልጁን ስለሚወደው።



አብርሃም ግን
ነገሩ ባይገባው እንኳ
እግዚአብሔርን መታመን
ያውቃል።



አብርሃምም በማለዳ
ተነሥቶ ሁለቱንም
ሎሌዎቹንና ልጁን
ይስሐቅን
ከእርሱ
ጋር ወሰደ።



እንጨትንም ለመሥዋዕት
ሰነጠቀ። ተነሥቶም
እግዚአብሔር
ወዳለው ቦታ ሄደ።




ከሶስት ቀናት በኋላ
ወደተራራው ደረሱ።
አብርሃምም ሎሌዎቹን
አላቸው፥ አህያውን
ይዛችሁ ከዚህ
ቆዩ እኔና ልጄ
ወደዚያ ሄደን
እንሰግዳለን፥
...


... ወደ እናንተም
እንመለሳለን። ይስሐቅ
የመሥዋዕቱን እንጨት
ያዘ፤አብርሃም
እሳቱንና
ቢላዋውን በእጁ
ያዘ፥ ሁለቱም
አብረው
ሄዱ።


ይስሐቅም አባቱን
አብርሃምን እሳቱና እንጨቱ
ይኸው አለ የመሥዋዕቱ በግ
ግን ወዴት
ነው? አለ።

አብርሃምም፦ ልጄ
ሆይ፥ የመሥዋዕቱን
በግ እግዚአብሔር
ያዘጋጃል
አለው።



እግዚአብሔር ወዳለውም ቦታ ደረሱ።
አብርሃምም በዚያ መሠዊያውን ሠራ።
ከዚህ ቀደም አብርሃም
መሰዊያን ሰርቷል። ይህ
ግን እጅግ ፈታኝ ነው።



እንጨትንም ረበረበ ልጁን ይስሐቅንም
አስሮ በመሠዊያው በእንጨቱ ላይ
አጋደመው። በእውነትም አብርሃም
እግዚአብሔርን በመታዘዝ
ልጁን ሊያርደው
ይሆን?





አዎ አብርሃምም
እጁን ዘረጋ፥
ልጁንም ያርድ
ዘንድ ቢላዋ አነሣ።
ልቡ እየመታ
ሊሆን ይችላል!



የእግዚአብሔር
መልአክ አብርሃምን
ጠራና፥-ተው! ተው!
እጅህን አትዘርጋ፤
አንድ ልጅህን ለእኔ
አልከለከልህምና።



እግዚአብሔርን
የምትፈራ እንደ
ሆንህ አሁን
አውቄአለሁ
አለ።


አብርሃምም አንድ በግ በዱር ውስጥ አየ። አብርሃምም ሄደ በጉንም ወሰደው፥በልጁም ፋንታ መሥዋዕት አድርጎ ሠዋው።


ይስሐቅ አባቴ እንዳለው
እግዚአብሔር የመስዋዕቱን
በግ አዘጋጅቷል ያለ
ይመስላል።

አብርሃምና ይስሐቅ እያመለኩ ሳለ እግዚአብሔር አብርሃምን፦ ቃሌን ሰምተሃልና። የምድር ሕዝቦች ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ አለው።



ይህም አንድ ቀን ኢየሱስ ከአብርሃም ዘር እንደሚመጣ ያመለክታል።




አብርሃምና ይስሐቅ ወደቤታቸው ተመለሱ።
ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሀዘን አጋጠመው።
ሚስቱ ሳራ ሞተች። አብርሃም ሚስቱን
አጣ፤ይስሐቅ ደግሞ
እናቱን
አጣ።

ሳራን ከቀበራት
በኋላ አብርሃም
ሎሌውን ለይስሐቅ ሚስት
እንዲፈልግለት ላከው።



ሎሌውም ወደ
አብርሃም ትውልድ
አገር በመሄድ ከዘመዶቹ ሚስት
ሊፈልግለት ተነሳ።



ሎሌውም ከእግዚአብሔር ምልክትን ጠየቀ፥-
ለግመሎቼ ውሀ የምትሰጠኝ እርስዋ ለባሪያህ
ለይስሐቅ ያዘጋጀሃት ሚስት ትሁን።



ወዲያውም ርብቃ ለግመሎቹ ሁሉ ውኃ ቀዳች። ሎሌውም ጸሎቱ እንደተሰማለት አወቀ።




ርብቃም ቤተሰብዋን ተሰናብታ ይስሐቅን ልታገባ ሄደች። ለይስሐቅም መጽናናት ሆነችለት።
ይስሐቅም በጣም ወደዳት።

# እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘፍጥረት 22-24

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ሰትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16